**MORESH WEGENIE AMARA ORGANIZATION**

**ሞረሽ ወገኔ የዐማራ ድርጅት**

8221 Georgia Avenue, Silver Spring, MD. 20910

**Tel: (202)-677-0094 Fax:**

**Web: http//www.moreshwegenie.org/**

ሞረሽ ወገኔ የዐማራ ድርጅት | አርብ ሚያዝያ ፲፮ ቀን ፪ሺህ፯ ዓ.ም. | ቅፅ ፫ ፣ ቁጥር ፲፬

# እረኛ የሌለው ከብት እና መሪ የሌለው ሕዝብ አንድ ናቸው

ባለፈው የአንድ ዓመት ጊዜ ውስጥ ከኢትዮጵያ ውጪ በሚኖሩ ኢትዮጵያውያን ላይ በተደጋጋሚ የደረሱባቸው ከፍተኛ ሰቆቃዎች አሉ። አምና በሣዑዲ ዓረቢያ፣ ባለፉት ሁለት ወራት ደግሞ በየመን በሚኖሩ የዕለት እንጀራ ፈላጊ በሆኑ በመቶ-ሺዎች በሚቆጠሩ ኢትዮጵያውያን ላይ የተጸፈመባቸው ግፍ የተሞላበት ግድያ እና ስቃይ፣ መንስዔው ኢትዮጵያ መሪ አልባ አገር በመሆኗ ነው። የደረሰው ሳይበቃ፣ በዚህ ምክንያትም ኢትዮጵያውያን ከደረሰብን መከራ ሳናገግም፣ ስቃዩ እና አሚሚቱ ከዐይናችን ሥር ሳይጠፋ፣ እናቶች የለበሱት የሐዘን ጨርቅ ሳይለወጥ፣ ሌላ መዓት በደቡብ አፍሪቃ በሚኖሩ መሪ አልባ ወንድም እና እህቶቻችን ላይ የተፈጸመው አሠቃቂ ግድያ የንብረት መውደም ተከተለ። **ሰሞኑን ደግሞ ኢትዮጵያዊ እና ክርስቲያን በመሆናቸው ብቻ፣ ፴(ሰላሣ) ኢትዮጵያውያን በሊቢያ እስላማዊ ጽንፈኞች እንደገና ጠቦት መታረዳቸውን በዘመኑ ቴክኖሎጂ ዐየነው ሰማነው። በእነዚህ ድርጊቶች መላው የሞረሽ ወገኔ ዐማራ ድርጅት አባሎች የተሰማን ስሜት በቃላት ይኸን ይመስላል ብሎ ለመግለጽ የሚያስቸግር ነው። በድርጊቶቹ ልባችን ደምቷል፣ እጅግ አዝነናል፣ ተክዘናል፣ ተናድደናል፣ ተቆጭተናል። የሞረሽ ወገኔ የዐማራ ድርጅት አባሎች እና ደጋፊዎች፣ ለሞቱት ወንድም እና እህቶቻችን አምላክ መንግሥተ ሰማያትን እንዲያወርስልን፣ ለተጎጂ ወገኖቻችን መጽናናትን እንዲሰጥልን የኀዘን ተካፋይነታችንን እንገልጻለን።**

**ሞረሽ ወገኔ የዐማራ ድርጅት፣ በሣዑዲ ዓረቢያ፣ በየመን፣ በደቡብ አፍሪቃ እና በሊቢያ በኢትዮጵያውያን ላይ ለተፈጸመው እጅግ ዘግናኝ እና አሠቃቂ ግድያ የድርጊቱ ፈጻሚዎች የየተጠቀሱት አገሮች መንግሥታት እና ዜጎች ስለሆኑ ቀዳሚ ኀላፊነቱ የእነርሱ እንደሆነ ያምናል። ሆኖም እንዲህ ዓይነት ድርጊቶች በኢትዮጵያውያን ላይ እንዲፈጸሙ፣ ኢትዮጵያውያን በዓለም ላይ የነበረንን ክብር እና ዝና አዋርዶ ለዚህ ዓይነቱ ጥቃት ያጋለጠን፣ አንድነት እና ሰላማችን አሳጥቶ ለስደት እና ለመከራ የዳረገን፣ የትግሬ-ወያኔ ዘረኛ አገዛዝ እና የሥርዓቱ አራማጆች መሆናቸውን ልብ ልንል እንደሚገባ ሞረሽ-ወገኔ ለማስገንዘብ ይወዳል። እነዚህ በሊቢያ እስላማዊ ጽንፈኞች የተገደሉ ወንድሞቻችን ኀይማኖታቸው ምንም ይሁን ምን፣ የታረዱበት ምክንያት «ክርስቲያን ናችሁ» የሚል በመሆኑ ብቻ ለኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ኀይማኖት ሰማዕታት ናቸው ብሎ ሞረሽ-ወገኔ በጽኑ ያምናል። ስለዚህም ዘወትር ሕዝበ ክርስቲያኑ በፀሎቱ ሊያስባቸው፣ በኀይማኖቱ ሥርዓትም አስፈላጊው የፍትኀት መታሰቢያ ሊደረግላቸው እንደሚገባ ሞረሽ-ወገኔ በአፅንዖት ያሳስባል።**

ኢትዮጵያውያን በዛሬው ዘመን ሥቃይ እና መከራ ለሚቀበሉባቸው አገሮች ሕዝብ፣ በታሪክ ወደኋላ ሄዶ እኛ ምን ዓይነት በጎ ተግባር እንደፈፀምንላቸው ማውሣት ይቻላል። ዛሬ ኢትዮጵያውያን ክርስቲያኖችን በአሰቃቂ ሁኔታ የሚያርዱት እና በጥይት ደብድበው የሚገድሉት ሊቢያውያን፣ ከ፪ኛው የዓለም ጦርነት ማግሥት በኋላ ለሦሥት ተከፋፍለው (ትሪፖሊታኒያ፣ ፌዛን እና ሴሬናይካ) በጣሊያን፣ በፈረንሣይ እና በእንግሊዝ ቅኝ ግዛትነት እንዲገዙ የኃያላን መንግሥታት ፍላጎት እና ዕቅድ ነበር። ሆኖም ታላቁ ኢትዮጵያዊ ዲፕሎማት እና ፖለቲከኛ ፀሐፌ-ትዕዛዝ አክሊሉ ኀብተወልድ እና አጋሮቻቸው ባደረጉት ከፍተኛ ዲፕሎማሲያዊ ትግል ሊቢያ ከታሰበላት የዳግም ቅኝ አገዛዝ ሤራ ነፃ ለመውጣት በቃች። የዛሬን አያድርገውና፣ ኢትዮጵያውያንን የመኪና ጎማ በአንገታቸው እያጠለቁ የሚያቃጥሉት ደቡብ አፍሪቃውያን፣ በአፓርታይድ አገዛዝ ሥር በነበሩበት ዘመን፣ ከሚቹ መሪያቸው ከፕሬዘዳንት ኔልሰን ማንዴላ ጀምሮ እስከ ተራ የአፍሪቃ ብሔራዊ ኮንግረስ ተዋጊዎች እና ቤተሰቦቻቸው ድረስ የኢትዮጵያውያን የተከበሩ እንግዶች ነበሩ። ከ፲፱፻፶ዎቹ አጋማሽ በኋላ በነዳጅ ሽያጭ ገንዘብ ናላቸው የዞረው አረቦች፣ ከ፷(ስድሣ) ዓመታት በፊት በገፍ በሚሰደዱበት ዘመን በቅድሚያ መጠለያቸው ኢትዮጵያ ነበረች። **«ወርቅ ላበደረ ጠጠር፣ እህል ላበደረ አፈር» ሆነና ዛሬ ኢትዮጵያውያን በዓለም በየትኛውም ክፍል በስደት ለመኖር እንኳን የማንችልበት ደረጃ ላይ ደርሰናል።** ስለሆነም ለሚደርሱብን የግፍ ጥቃቶች ምክንያቶቹን መርምረን ተገቢ እርምጃዎችን መውሰድ የእኛ የዘመኑ ኢትዮጵያዊ ትውልድ ኃላፊነት ነው።

በታሪካችን ኢትዮጵያውያን እንደዚህ ዘመኑ ያለ መረገጥ እና መጨቆን፣ መከራ እና ስቃይ፣ ውርደት እና መናቅ፣ መንቋሸሽ እና ከሰውነት በታች መታየት፣ ስደት እና መንከራተት፣ ወዘተርፈ ገጥሞን አያውቅም። አውቀነውም ይሁን ሳናውቀው፣ አምነንም ሆነ ተገደን፣ ለዚህ ሁኔታ በራሳችን ላይ መድረስ እያንዳንዳችን የየበኩላችንን አስተዋጽኦ አድርገናል። እንደ ሰንበት ጠበል ጸዲቅ በቋንቋ ሲሸነሽኑን፣ ታሪካችን ሲደልዙ፣ ባሕላችን ሲያንቋሽሹ፣ አንድነታችን ሲንዱ፣ የወል እሴቶቻችን ሲያወድሙ «ኧረ-ለምን?» አላልንም። የትግሬ ነገድ ልሂቃን ዘመን ጠገብ ታሪካችንን በመቶ ዓመት ሲገድቡ፣ ኤርትራን አስገንጥለው አገራችንን ወደብ አልባ ሲያደርጉ፣ ድንግሉን መሬታችን ለሱዳን በገጸ-በረከትነት ሲቸሩ፣ በአጠቃላይ ለ፳፬(ሃያ አራት) ዓመታት በአገሪቱ እና በሕዝቡ ዕጣ-ፋንታ ላይ

እንዲወስኑ ዕድሉን ሰጥተናቸዋል። በዚህ ጊዜ ውስጥ ለፈጸሙት ማናቸውም ነገር የተቀነባበረ እና የተዋሐደ፣ ወጥ የተቃውሞ እና የእምቢተኝነት ስሜት አላሣየንም። ስለዚህ ይህ በሣዑዲ ዓረቢያ፣ በየመን፣ በደቡብ አፍሪቃ እና በሊቢያ በወንድሞቻችን እና በእህቶቻችን ላይ የተፈጸመው ግፍ እንዲፈጸም የራሣችን ቸልተኝነት የበኩሉን አስተዋጽዖ አላደረገም ለማለት አይቻልም።

ከሁሉም በላይ በሐረርጌ፣ በአርሲ፣ በወለጋ፣ በኢሉባቡር፣ በወልቃይት፣ በጠገዴ፣ በጠለምት፣ በሰቲት እና በሌሎችም የኢትዮጵያ ክፍሎች የዐማራ ነገድ አባሎች የሴቶች ጡት ሲቆረጥ፣ የወንዶች ብልት ሲሰለብ፣ ከነሕይዎታቸው ወደ ገደል ሲጣሉ፣ እርጉዞች ሆዳቸው ተቀድዶ ሽል ሲሰለብ፣ ማንም ከቁብ የቆጠራቸው የለም። በመተከል (ጉምዝ) እና በአሶሳ (ቤንሻንጉል)፣ በጉራ ፈርዳ፣ በወለጋ፣ በአምቦ እና አካባቢው፣ በአርሲ ነገሌ፣ ወዘተርፈ ነዋሪ በነበሩ ዐማሮች ላይ ዐማራ በመሆናቸው ብቻ ተነጥለው፣ በዘመን ፍሰት ያፈሩትን ሀብት እና ንብረት «ደጃፍ በመለሰ፣ ማጀት በጎረሰ» ተነጥቀው ሲባረሩ እና ለልምና እና ለችጋር ሲዳረጉ ያሰማነው ቃል አልነበረም። ስለሆነም «ሞት በእንቅልፍ ይለመዳል» እንዲሉ፣ የትግሬ-ወያኔ በኢትዮጵያ፣ በኢትዮጵያዊነት፣ በዐማራ እና በኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ኃይማኖት ላይ ያለውን እጅግ የከረረ ጥላቻ በፕሮግራም ነድፎ የተሰለፈ መሆኑን በተጋጋሚ እየነገረን እና እያወቅን፣ «ልክ አይደለህም» የማለቱ ወኔው እና ቁርጠኝነቱ አንሶን፣ ዛሬ «እሪ! ድረሱልን!» ለምንልለት መከራ ደርሰናል።

የቦታ፣ የገዳዮች፣ እንዲሁም የተገዳዮች ማንነት እና ቁጥር ከመለያየቱ በስተቀር፣ በሣዑዲ ዓረቢያ፣ በየመን፣ በደቡብ አፍሪቃ እና በሊቢያ በኢትዮጵያውያን ላይ የተፈጸመው ግድያ እና የደረሰባቸው ስቃይ፣ የትግሬ-ወያኔ በዐማራው ነገድ ተወላጆች ላይ ካደረሰው የተለየ አይደለም። **ባለፉት ፳፬(ሃያ አራት) ዓመታት ብቻ የትግሬ-ወያኔ ከ፭(አምሥት) ሚሊዮን የማያንሱ ዐማሮችን ከምድረ-ገፅ አጥፍቷል። ከዚህ ቁጥር ውስጥ ግማሹን (2.5 ሚሊዮን) ያህል ዐማራዎችን ማጥፋቱን የትግሬ-ወያኔ በራሱ ፓርላማ ተብዬ አምኗል።** ከእኒህ ውስጥ በአሰቦት ገዳም፣ በበደኖ፣ በአርባ ጉጉ፣ በወተር፣ በአረካ ወዘተርፈ የትግሬ-ወያኔ በዐማራው ነገድ ላይ የፈጸመውን ግፍ በዐይናችን እያየን፣ በጆሮአችን እየሰማን፣ ስለድርጊቱ ከተለያዩ ዘገባዎች እያነበብን፣ ዝምታን፣ አልፎ አልፎም «እንኳን ደግ አደረገ» እያልን መከራውን መላመዳችንን መካድ የለብንም። በመሆኑም ኢትዮጵያውያን «ከመሞት መሰንበት» ብለው በሚሊዮኖች ወደውጪ አገሮች ለመሰደድ ተገድደዋል። መሰደድም እንደ ቅንጦት ተቆጥሮብን ይኼውና ዛሬ ዘር ሳይለይ ሁሉንም ተሰዳጅ ኢትዮጵያውያን፣ ኢትዮጵያዊ በመሆናችን ብቻ በዚህ ፳፩ኛው(ሃያ አንደኛው) ክፍለዘመን ይፈጸማል ተብሎ ለማይገመት ጥቃት ተጋላጭ እንድንሆን አድርጎናል። አጋላጫችን ማንም ሳይሆን የትግሬ-ወያኔ አገዛዝ ነው። ስለሆነም የወያኔ ትውልድ እና እምነት ተከታዮች በኢትዮጵያ በፖለቲካ ሥልጣን ላይ እስካሉ ድረስ፣ በኢትዮጵያውያን ላይ የሚፈጸሙት እንዲህ ዓይነት ድርጊቶች መቼም ይቆማሉ ብሎ ሞረሽ ወገኔ የዐማራ ድርጅት አያምንም።

በመጽሐፍ ቅዱስ እንደተጻፈው፣ ኢየሱስ ክርስቶስ ሲያስተምር፣ መቶ በጎች ያሉት እረኛ፣ ካሉት በጎች አንዷ ብትጠፋው፣ ዘጠና ዘጠኙን ትቶ፣ የጠፋችውን አንዷን በግ ፍለጋ መሄዱን ነው። ብዙ ንብረት አለኝ ተብሎም ጥቂቱ እንዲጠፋው የሚፈልግ ማንም ሰው የለም። መጀመሪያ እንዳይጠፋ ጥበቃ እና ጥንቃቄ ይደረጋል። ይህ ሁሉ ተደርጎም የመጥፋት አጋጣሚ ከተፈጠረ፣ የጠፋውን ለማግኘት መፈለግ የተለመደ ነው። ይህ በዓለማዊውም ሆነ በመንፈሣዊ ሕይዎት እና ኑሮ የተለመደ የመልካም እረኛ ተግባር ነው። ሰነፍ እረኛ መንጋውን አንድም ለአራዊት፣ ሁለትም ለርሃብ እና ለውኃ ጥም ያጋልጣል። የጠፉትንም መንጋዎች ለመፈለግ እጅግም አይጥርም። ከጅምሩ ሰነፍ ነውና ለጥፋት እንጂ፣ ለጥበቃ ዝግጁ ባለመሆኑ! ብሔራዊ ስሜት፣ የሕዝብ ፍቅር እና አመኔታ የሌለው ገዢም በሕዝብ ጫንቃ ላይ ሲወጣ፣ ገና ከጅምሩ በሕዝብ ፈቃድ እና ይሁንታ ለያዘው ኃላፊነት ያልበቃ በመሆኑ፥ ለጥፋት፣ ለሕዝብ መበደል፣ መገደል፣ መሰደድ፣ መታሰር፣ መሰቃየት፣ መራብ፣ መቸገር፣ ወዘተርፈ ግድ የለውም። እንዲያውም የጥፋቱ እና የችግሩ፣ የግድያው እና የእስራቱ፣ የስቃዩ እና የመከራው ዋና ተዋናይ እርሱ ይሆናል። ባለፉት ፳፬(ሃያ አራት) ዓመታት የትግሬ-ወያኔ በዘረጋው የዘረኝነት ፖለቲካ ምክንያት፣ ኢትዮጵያውያን በአገራችን የመኖር እና የመሥራት መብቶቻችን ተነጥቀናል። ስለዚህም ኢትዮጵያውያን የሚደርስብን መሳደድ፣ መገደል፣ መዋረድ፣ በየትም ቦታ ከአጥፊ እንስሳዎች በታች በሆነ ሁኔታ መታረድ፣ በበረሃ እና በውቅያኖስ ውስጥ የየብስ እና የባሕር አራዊት ቀለብ መሆን ዕጣ ፋንታችን ሆኗል። ለዚህ ሁሉ ያበቁን መልካም መሪ መሆን ቀርቶ፣ ክፉ ጎረቤት ለመሆን የማይበቁ ሰዎች በአገሪቱ እና በሕዝቡ ጫንቃ ላይ በመውጣታቸው ነው።

የተከፋፈለ ሕዝብ ምንጊዜም ለጠላቶቹ በቀላሉ ተጠቂ ነው። እኛ ኢትዮጵያውያን የሚደርስብን ጥቃት በዕውነት ከመረረን፣ ከጥቃት መውጣት የምንችለው የትግሬ-ወያኔ የሰረቀንን አንድነት መልሰን ስንረከብ ነው። ለወደፊትም በኢትዮጵያውያን ላይ ተመሣሣይ ጥቃት እንዳይፈጸም፣ ስደት እና ሥቃይ እንዲቆም፣ ብሔራዊ ውርደት ተወግዶ በመካከላችን የነበረው የጥንቱ የአንድነት እና የአብሮነት ስሜት እንዲጎመራ፣ የመከራችን እና የስቃያችን ቀፍቃፊ፣ የእኛነታችን ፀር የሆነው የትግሬ-ወያኔ አገዛዝ መወገድ አለበት ብለን እናምናለን። ሠሞኑን የአዲስ አበባ ነዋሪዎች በሠላማዊ ሰልፍ ላይ እንዳሉት፦ **«መሪ የሌለው እዚህ [ኢትዮጵያ] ብቻ ነው»**። ስለዚህ ኢትዮጵያውያን ከገባንበት የታሪክ ማጥ ለመውጣት መልካም እና ቅን ኢትዮጵያዊ መሪ ሲኖረን ይገባል። ለዚህም በግፍ በባዕድ አገር ደማቸው የፈሰሰው የንፁሐን ሰማዕታት ዜጎቻችን አምላክ ይርዳን። «ሁሉም ነገር ለበጎ ነው» የሚባል ነገር አለና፣ የደረሰብን ይህ ሁሉ ክፉ እና አሰቃቂ ድርጊት፣ የእኛን ኅብረት እና አንድነት መልሶ በማጎናጸፍ፣ መከራ እና ስቃይ፣ ስደት እና ዋይታ፣ ብሔራዊ ውርደት ታሪክ የሚሆኑበትን መንገድ ሁላችንም በያለንበት እንድንጠርግ አደራ እንላለን።

**ኢትዮጵያ በታማኝ እና ቆራጥ ልጆቿ መስዋዕትነት ለዘለዓለም ፀንታ ትኖራለች!**